# የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር
## ማዕከላዊ ኮሚቴ
## (ኢ.አአግማኮ)

እንድ ሀገር
አንድ ሕዝብ
አንድ ሰንደቅ ዓላማና
አንድ የጋራ ዕድል

ONE COUNTRY
ONE PEOPLE
ONE FLAG & ONE
COMMON DESTINY

## ETHIOPIAN UNITY PATRIOTS FRONT CENTRAL COMMITTEE
## (EUPFCC)

ቅፅ 001/1999 ጥቅምት 20 ቀን 1999

# ከኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር (ኢ.አአግ) ማእከላዊ ኰሚቴ የተሰጠ መግለጫና ጥሪ

የዘመናት አኩሪ ታሪክ ባለቤት የሆነችው ውድ ሀገራችን ኢትዮጵያ በሀገር ክሕደት ከታሪክና ከትውልድ ባፈነገጡ ሐይሎች እጅ ወድቃለች።

ሕዝባችን በአምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ታስሮ የመናገር፣ የመፃፍ የመሰብሰብና ሌሎች ሰብዓዊ መብቶቹን ተገፎ እጅግ ለመግለፅ በሚያስቸግር የመከራ ሕይወት ውስጥ ይገኛል።

ወያኔው ከምንጊዜውም በላይ በጠባብ የዘረኝነትና የጐሰኝነት ፖሊሲ በመንቀሳቀስ ሕዝባችንን በመግደልና በማሰር አቻ የማይገኝለት ወንጀል እየፈፀመ ነው ፡ የየዕለት ሙያውና ተግባሩ አድርጐም ቀጥሎበታል። በተለይም ደግሞ የተቃዋሚው ሐይል በጋራ አብሮ ለመንቀሳቀስ ባለመቻሉ የተነሣ ወያኔው ጊዜ አግኝቶና ጊዜ ወስዶ እንደአሻው እንዲሆን አስችሎታል።

በእርግጥ ተቃዋሚው ሐይል በራሱ በአንድ ወገን በጠባብ ብሔርተኝነትና በሌላ ወገን በትምክህተኝነት ዙሪያ የተሰባሰበ በመሆኑ ልዩነቶችን ለማስታረቅና ሆነ ለማቻቻል አልተቻለም። የተደረገው ሙከራ ሁሉ ፋይዳ ስለአልነበረው በፀረ-ወያኔ ትግሉ ወስጥ ያደረገው አስተዋፅኦ ከቁጥር የሚገባ አይደለም። ችግሩ አሁን ድረስ መፍትሔ አላገኘም። ይህ ደግሞ ምን ያህል የሕዝባችንን አንገት አስደፍቶ ለወያኔው ጥቃት እንደአጋለጠው በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

ተቃዋሚ ሐይል ቀደም እንደነበረውና አሁን በሚታየው ሁኔታ ከቀጠለ ወያኔውን ለማስወገድ ቀርቶ ለማንገዳገደም የሚያዳግት ይሆናል።

በእኛ በኩል ከሌሎች ተቃዋሚ ሐይሎች ጋር በሕብረትም ይሁን በውሕደት ለመስራት ተንቀሳቅሰናል የአንዳንዶቹ ባሕሪይ የማይጨበጥና የአንዳንዶቹ ደግሞ ኰሚቴ ከመመስረት ያለፈ ራዕይ የሌላቸው በመሆኑ ጥረታችን አልተሳካም።

በፀረ-ኢትዮጵያ ሐይሎች ስብስብ ውስጥም መደባለቁ የወያኔን የከፋፍለው ግዛው ፖሊስና የጠባብ ብሔርተኝነት ስሜት ናፋቂ እንደመሆን ይቆጠራል። ይህ ደግሞ ከተነሣንለት ሕዝባዊ አላማ ጋር በፍፁም የሚፃረር ነው።

የእኛ ዓላማ ከመነሻውም ግልፅ ነው ።እጅግ የሚገርመው ጉዳዩ ደግሞም አንዳንዶቹ ማንነታችንና ምንነታችን በትክክል እያወቁ የተሳሳተና መሰረት ቢስ የውሸት ፕሮፓጋንዳ

በማናፈስ የሌለና ተስፋ ቢስ የሆነ ርካሽ ተወዳጅነት ሲባዝኑ ይታያሉ። የተሻሉ ሆነው የማድረጉ አቅሙ ካላቸው ደግሞ ሙሉ ጊዜያቸውን በእኛ ላይ ሳያጠፉ ከእሩቅ ተመልካችነት እራሳቸውን ስበው ወደ መስክ ቢወርዱ ይበጃል እንላለን። ከዚህ ውጪ ግን ጥቅሙ ለፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ብቻ ነው።

ውድ ኢትዮጵያውያን

የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር (ኢአአግ) በፀረ-ወያኔ የአርበኝነት ትግሉ ውስጥ መንቀሣቀስ ከጀመረ የቆየ ቢሆንም በተለያዩ ወቅቶቶች ባጋጠመው ሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት ብዙ መራመድ ሳይችል ቆይቷል። ይሁን እንጅ አቅም በፈቀደው መጠን ጣምራ ተግባራትን አከናውኖአል።

በተለይም ግንባሩ እራሱን በውጭው ዓለም ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ለማስተዋወቅ ያደረግነው ጥረትና በዚህ ሒደትም ለኢአአግ ጥንካሬና የትግል ስምሪት በርካታ ኢትዮጵያውያን ያሳዩት ተሳትፎ የሚያበረታታ ነበር ። በአንፃሩ ደግሞ የተቀዋሚው ሐይል እንደፈተለገው በሕዝባዊ ትግሉ ወስጥ ዘልቆ ያለመገኘት የብዘዎቹን ሕሊና እንደጐዳና መሰላቸትን እንደፈጠረ መገንዘብ ችለናል።

የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር (ኢአአግ)

- ለአንድ ሃገር
- ለአንድ ሕዝብ
- ለአንድ ሰንደቅ ዓለማና ለአንድ የጋራ ዕድል እውን መሆን የገባውን ቃል ኪዳን ሳያጥፍ ያሉትን አጠቃላይ ሁኔታዎች ከገመገመና ካጤነ በኃላ የትጥቅ ትግሉን ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ ለማቀጣጠልና ለወያኔው ግብዓተ መሬት መቃረብ አስፈላጊወን ሁሉ በማድረግ ላይ ይገኛል። የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞት ግንባር ሠራዊት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ትግሉን ለማጧጧፍ በታግሎ አትጋይነት ተሰልፏል።

ውድ ኢትዮጵያዊያን

ሕዝባችን አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ እስከ ዛሬ ድረስ በአደረሰበት ጭቆናና አፈና እንዲሁም ይህን ጭቆናና አፈና ለመገርሰስ በተቃዋሚ ሐይሎች በኩል በሚታየው መጠላለፍ ሳይሸማቀቅ፣ እና ስሜቱን ሳይጐዳ ወገቡን አጥብቆ ከኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር (ኢአአግ ) ጐን መሰለፍ ይጠበቅበታል።

ይህን ትግል በድል አድራጊነት ለመደምደም እንበቃ ዘንድም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የላብና የጊዜ መስዋእትነት ከመክፍል ባሻገር ከእለት ጉርሱ ጭምር ቀንሶ በሚያልፍ ሕይወት የማያልፍ ታሪክ ለመስራትና እኛም ለጀመርነው የተጋድሎ ታሪክ ውጤታማነት ሕዝባዊ ድጋፋችሁ ያስፈልገናል።

ይህ ትግል ሕዝባዊ እንደመሆኑ መጠን ሕዝበዊ ድጋፍና ሕዝባዊ ተሳትፎ ያስፈልገዋል። በተለይም በውጭው ዓለም የምትገኙ ወገኖቻችን እኛ ሕይወት ልንከፍልበት የተነሣልንለትን ዓላማ በቁሳዊ ድጋፍና በዓላማ ፅናት እንድትአጅበት እንጋብዛችኃለን ኢትዮጵዊነት እንዲቀጥል ኢትዮጵያ መኖር አለባት ለጋራ ሐገራችንና ለጋራ ቤታችን ሁላችንም አቅማችን በፈቀደው መሠረት በጋራ እንድንቀሳቀስ ወገናዊ ጥሪአችንን እናቀርባለን። በአውሮፓና በአሜሪካ እንዲሁም በሌሎች አካባቢዎች ከሚገኙ የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር (ኢአአግ) አስተባባሪዎች፤አባላትና ደጋፊዎች ጋር በመቀናጀት በፀረ-ወያኔ የአርበኝነት ትግሉ ወስጥ የነቃ ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጠይቃችኃለን።

የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር (ኢአአግ)

- የጥቁር አንበሳ
- የቴዎድሮስ
- የምኒልክ
- የአዋሽ ሠራዊት ጥንስሶች ከሕዝባችን የሚሰጠውን ሕዝባዊ ድጋፍ ምርኩዝ በማድረግ ታሪካዊ ግዴታቸውን ለመወጣት ዝግጁ መሆናቸውን በአክብሮት እንገልፃለን ። ትግሉ አጭር ድሉ እሩቅ ሳይሆን ቅርብ ነው።

ሰልፍ የጀግና ድል የእግዚአብሔር ነው

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር

የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር (ኢአአግ)

ማእከላዊ ኰሚቴ